# ለስደተኝነት መታወቂያ (ሪፍዪጂ አይ ዲ) ወይም ስደተኝነት የጉዞ ሰነድ (ፓስፖርት) በኦንላይን ማመልከት የምችለው እንዴት ነው?

ይህ ሰዎች በደቡብ አፍሪካ ያለውን የጥገኝነት አሠራር ሥርዓት እንዲረዱ የሚያግዝ ሰነድ ነው። እባክዎን ይህ መመሪያ ብቻ እንጂ በሕግ የተደነገ ምክር አለመሆኑን ይገንዘቡ። ይህ መረጃ ሊቀየር ስለሚችል ራስዎን በመረጃ ለማዘመን ይህን ድረ-ገጽ ይመልከቱ: www.scalabrini.org.za/information-about-asylum-in-south-africa።

በዚህ ሰነድ ላይ ተመስርተው ለሚወሰዱ እርምጃዎች በኬፕታውን የሚገኘው የስካሊብሪኒ ማዕከል ኃላፊነቱን አይወስድም።

## እባክዎትን ልብ ይበሉ፤

የስደተኝነት ማረጋገጫ ወረቀት (Refugee Status) ሕጋዊ ሰነድ መሆኑን ልብ ይበሉ። ከስደተኝነት ማረጋገጫ ወረቀት (Refugee Status) በተጨማሪ ለስደተኝነት መታወቂያ (Refugee ID) ወይም ሪፍዩጂ የጉዞ ሰነድ (ፓስፖርት) ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ። የስደተኝነት የጉዞ ሰነድ (ፓስፖርት) ማመልከቻ ማስገባት የሚችሉት ግን የስደተኝነት ስታተስ ሰነድ ወይም ወረቀት (Refugee Status) ካገኙ በኋላ ብቻ ነው። የሪፍዩጂ መታወቂያ (Refugee ID) ሰነድ ማለት ባለ ዐሥራ ሦስት አሃዝ (digit) ያለው የመታወቂያ ሰነድ ነው። ለሪፍዩጂ መታወቂያ (Refugee ID) አመልክተው ሰነዱን ካገኙ በኋላ ለሪፍዩጂ የጉዞ ሰነድ (ፓስፖርት) ማመልከት ይችላሉ።

### ደረጃ ፩፤




**የግል ኢሜይል አካውንት እንዳለዎት እርግጠኛ ይሁኑ**

### ደረጃ ፪፤



**ለሀገር ውስጥ ጉዳዮች መሥሪያቤት (DEPARTMENT OF HOME AFFAIRS) ኢሜይል ይላኩ**

### ደረጃ ፫፤



**ምላሽ ይጠብቁ። የቀጠሮ ደብዳቤ በኢሜይልዎ ይላክልዎታል።**



**በቀጠሮው ዕለት ወደ የጥገኝነት ጥያቄ መቀበያ ቢሮ (REFUGEE RECEPTION OFFICE) ሄደው ለሪፍዩጂ መታወቂያ (REFUGEE ID) ወይም ሪፍዩጂ የጉዞ ሰነድ (ፓስፖርት) ማመልከቻዎን ያስገቡ።**

ዝርዝር መረጃዎችን በሚቀጥሉት ገጾች ይመልከቱ

Scalabrini
Centre of Cape Town

## ደረጃ ፩፤ የግል ኢሜይል አካውንት እንዳለዎት እርግጠኛ ይሁኑ

ለሪፍዩጂ መታወቂያ ወይም ሪፍዩጂ የጉዞ ሰነድ (ፓስፖርት) ማመልከቻ ሂደትዎን ለመጀመር የግል ኢሜይል አካውንት መኖር በጣም አስፈላጊ ነው። የግል ኢሜይል አካውንት ከሌልዎ ማውጣት ግዴታዎ ነው። የኢንተርኔት ካፌዎች የሚጠቀሙባቸውን ኢሜይል አካውንቶች እንዲሁም ከሌሎች ጋር የሚጋሯቸውን ኢሜይል አካውንቶች ለዚህ ሂደት አይጠቀሙ፤ ይህ የግልዎ ኢሜይል አካውንት መሆን አለበት። ይህን አካውንት ወደፊት ስለሚጠቀሙበት፣ የመግቢያ ዝርዝር (log in details) እና የይለፍ ቃላቶች (password) ሊያስታውሷቸው የሚችሏቸው ዓይነት መሆናቸውን ያረጋግጡ። በአሁኑ ወቅት የሀገር ውስጥ ጉዳዮች መሥሪያቤት (Department of Home Affairs) የሚሰጣቸው አብዛኞቹ አገልግሎቶች የሚሰጡት በኦንላይን ነው። ከሀገር ውስጥ ጉዳዮች መሥሪያቤት (Department of Home Affairs) ጋር ግንኙነት ለማድረግ ከላይ የተጠቀሰውን የግል ኢሜይል አካውንትዎን እንዲጠቀሙ እንመክራለን።

## ደረጃ ፪፤ ለሀገር ውስጥ ጉዳዮች መሥሪያቤት *(DEPARTMENT OF HOME AFFAIRS)* ኢሜይል ይላኩ


ለሪፍዩጂ መታወቂያ (ለሪፍዩጂ አይ ዲ) ወይም ሪፍዩጂ የጉዞ ሰነድ (ፓስፖርት) ለማመልከት፣ ኢሜይል በመላክ ሂደቱን ይጀምሩ። ሆኖም በሂደቱ የኋለኛ ምዕራፍ በሚሰጥዎ ቀጠሮ መሰረት ወደሚመለከተው የጥገኝነት ጥያቄ መቀበያ ቢሮ (Refugee Reception Office) በመሄድ በአካል መገኘት ይኖርብዎታል። የሚልኩት ኢሜይል በሚከተሉት የኢሜይል አድራሻዎች መሆኑን ያረጋግጡ።

| | |
|---|---|
| ለሪፍዩጂ መታወቂያ ሰነድ **(ID)** ለማመልከት በዚህ አካውንት ይላኩ፤ | **refugeeID@dha.gov.za** |
| ከሪፍዩጂ መታወቂያ **(ID)** ማመልከቻዎ ጋር በተያያዘ ላለዎት ጥያቄ ይህን ኢሜይል ይጠቀሙ፤ | **enquiryRefugeeID@dha.gov.za** |
| ለሪፍዩጂ የጉዞ ሰነድ **(**ፓስፖርት**)** ለማመልከት በዚህ አካውንት ይላኩ፤ | **traveldoc@dha.gov.za** |
| ከሪፍዩጂ የጉዞ ሰነድ **(**ፓስፖርት**)** ማመልከቻዎ ጋር በተያያዘ ላለዎት ጥያቄ ይህን ኢሜይል ይጠቀሙ፤ | **enquirytraveldoc@dha.gov.za** |
| የሪፍዩጂ መታወቂያ ወይም የሪፍዩጂ የጉዞ **(**ፓስፖርት**)** ሰነድዎን ለመውሰድ በሚከተለኡት አድራሻ ኢሜይል ይላኩ | |
| ፕሪቶሪያ፤ | **collectionDTRRO@dha.gov.za** |
| ደርባን፤ | **collectionDurban@dha.gov.za** |
| መሲና፤ | **collectionMusina@dha.gov.za** |
| ኬፕታውን፤ | **collectionCTRRO@dha.gov.za** |
| ሔበርሃ (ፖርት ኤልዛቤት)/ **GQEBERHA / PORT ELIZABETH**፤ | **collectionPERRO@dha.gov.za** |

- እባክዎን ልብ ይበሉ፤ የሀገር ውስጥ ጉዳዮች መሥሪያቤት **(Department of Home Affairs)** የሚሰጠውን አደግልግሎት ለማሻሻል ይህን የኢሜይል አካውንት መጠቀሙን ለማቆም ወስኗል - **enabledocument.asm@dha.gov.za**
- ከዚህ ቀደም እስከ ሴፕቴምበር **30** ድረስ በዚህ ኢሜይል አካውንት ማመልከቻ አስገብተው ከሆነ፣ **እንደገና ማመልከት አያስፈልግዎትም።** በእነዚህ ጊዜያት ያስገቧቸው ማመልከቻዎች በሂደት ይታዩልዎታል።

## ለሪፍዩጂ መታወቂያ (REFUGEE ID) ለማመልከት የሚያስፈልጉ ነገሮች

- **ከአንድ ዓመት ያላነሰ የ**«Formal Recognition of Refugee Status (Section 24 Visa)» **ሰነድ እውነተኛ ቅጂ**
- **የመኖሪያ አድራሻዎን የሚያሳይ ሕጋዊ ሰነድ**
- **ሰነዱን የወሰዱበትን ቢሮ የሚጠቁም ማስረጃ**
- **በኢሜይል ሰሌዳው ላይ በሚገኘው የ**«Subject» **ሳጥን ውስጥ የሚከተለውን መረጃ በቅደም ተከተል ያስቀምጡ፤**





**Application for ID-Name of Refugee Reception Office (Names & Surname – File Number)**

ምሣሌ፤ **Application for ID – ደርባን (ሜሪ ንዳዎ – DBRSOM000121107)**

## ለሪፍዩጂ የጉዞ ሰነድ (ፓስፖርት) ለማመልከት የሚያስፈልጉ ነገሮች

፩) ለየጉዞ ሰነድ (Passport) ለማመልከት ከአንድ ዓመት ያላነሰ እውነተኛ ID ወረቀትዎን (ሰነድዎን) ቅጂ የያዘ ኢሜይል ይላኩ። ከዚሁ ኢሜይል ጋር ለማመልከቻዎ የሚረዱ እንደ (ያመለከቱበት ዩንቨርሲቲ ማመልከቻዎን መቀበሉን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ፣ የሥራ ቅጥር ደብዳቤ፣ ከሚሄዱት ተቋም የተላከ የግብዣ ደብዳቤ፣ ወዘተ) ያሉ ሰነዶችን ጨምረው ይላኩ።
፪) ኢሜይል ከላኩ በኋላ ወደሚመለከተው የጥገኝነት ጥያቄ መቀበያ ቢሮ (Refigee Reception Office) የሚሄዱበትን የቀጠሮ ቀን የያዘ የኢሜይል ምላሽ ይላክልዎታል።
፫) በቀጠሮው ቀን ጉዳይዎን ለመከታተል በሚሄዱነት ጊዜ ከሁለት የፓስፖርት ፎቶግራፍ ጋር ሌሎች አባሪ ሰነዶችዎን ይዘው ይሂዱ። ለፓስፖርት ማመልከቻ ክፍያው 600 ራንድ ነው።

በኢሜይል ሰሌዳው ላይ በሚገኘው የ«Subject» ሳጥን ውስጥ የሚከተለውን መረጃ በቅደም ተከተል ያስቀምጡ፤




**Application for Travel Document-Name of Refugee Reception Office (Names & Surname – File Number)**

ምሣሌ፤ **Application for Travel Document – Desmond Tutu (ኢቲኔ ንድዙቤ – PTACOD0020121106)**

## ደረጃ ፫፤ ምላሽ ይጠብቁ። የቀጠሮ ደብዳቤ (ወይም ወረቀት) በኢሜይልዎ ይላክልዎታል። በቀጠሮው ዕለት ወደቦታው ይሂዱ።

ለሀገር ውስጥ ጉዳዮች መሥሪያቤት (Department of Home Affairs) ኢሜይል ከላኩ በኋላ፣ የቀጠሮውን ቀን የያዘ ኢሜይል መልሰው ይልኩልዎታል። ይህ የተወሰነ ጊዜ ሊወስድ ይችላል። የቀጠሮ ደብዳቤው ከሚላከው ኢሜይል ጋር ይያያዛል። ደብዳቤው ወደ የጥገኝነት ጥያቄ መቀበያ ቢሮ (Refugee Reception Office) መቼ መሄድ እንዳለብዎት ይገልጻል።

- በቀጠሮው ዕለት ወደ የጥገኝነት ጥያቄ መቀበያ ቢሮ (Refugee Reception Office) መሄድዎን እንዳይረሱ
- በቀጠሮው ዕለት የሪፍዩጂ ስታተስ ወረቀትዎን ይዘው ይሂዱ
- በቀጠሮው ቦታ ለሪፍዩጂ መታወቂያ ወይም ለሪፍዩጂ የጉዞ (ፓስፖርት) እና ለሪፍዩጂ መታወቂያ የሚያስፈልገውን ቀሪ የማመልከቻ ሂደት ያጠናቅቃሉ። ይህንኑ የሚያረጋግጥ ደረሰኝ ይሰጥዎታል።
- ከተወሰነ ጊዜ ባኋላ የሪፍዩጂ መታወቂያ ወይም/እና የሪፍዩጂ የጉዞ ሰነድ (ፓስፖርት)ዝግጁ መሆናቸውን የሚገልጽ ኢሜይል ወይም አጭር መልእክት ይደርስዎታል። ከዚህ በኋላ ወደቦታው ሄደው ሰነድዎን (ወረቀትዎን) መውሰድ ይችላሉ።

## የቀጠሮ ደብዳቤ አልደረሰኝም። ምን ማድረግ ነው ያለብኝ?

**ለሪፍዩጂ መታወቂያ ወይም ሪፍዩጂ የጉዞ ሰነድ (ፓስፖርት) የሚደረጉ ማመልከቻዎች ረጅም ጊዜ ይወስዳሉ። የቀጠሮውን ርዝመት የሚወስኑት የጥገኝነት ጥያቄ መቀበያ ቢሮዎች (Refugee Reception Office) ሳይሆኑ ፕሪቶሪያ የሚገኘው የሀገር ውስጥ ጉዳዮች ዋና መሥሪያቤት (Department of Home Affairs in Pretoria) አሠራር ነው። እባክዎን በኢሜይል አካውንትዎ ውስጥ የሚገኙ «spam» እና «junk» ሳጥኖችን ማየትዎን እርግጠኛ ይሁኑ። የቀጠርዎ ደብዳቤዎን ከሦስት ወር በላይ ጠብቀው ከሀገር ውስጥ ጉዳዮች መሥሪያቤት ደብዳቤmካልደረስዎ፣ እባክዎ ጉዳዩን የሚመለከት ኢሜይል ይላኩ።**